# ፍኖተ ዴሞክራሲ የኢትዮጵያ አንድነት ድምፅ

Finote Democracy Voice of Ethiopian Unity

efdpu@aol.com www. Finote.org

**ፕሮግራም፦** ረቡዕና እሁድ ከምሽቱ ሁለት ሰዓት እስከ ሶስት ሰዓት በ 25 ሜትር ባንድ

**Program**: Wednesday and Sunday 8:00PM- 9:00 PM on 25 meter band.

## ዜና ዘገባ

**የከቲት 26 ቀን 2003 ዓ.ም.**

**- አፍለኛ እና ወጣት ካድሬዎች በወያኔ ላይ ጉድ አፈሉ፤**

**- ነጋዴው በወያኔ ትዕዛዝ ከውጭ ሀገር ምንም ዓይነት እቃ አናስገባም ሲል አቁዋም ያዘ፤**

**- 30 ብር ሲሸጥ የነበረው አንድ ኪሎ ቡና ከመቶ ብር በላይ አሻቀበ፤**

**- የወያኔው ከፍተኛ ባለስልጣን የነበረው ሀገር ጥሎ ወጣ፤**

**- ነባር መኮንኖች ጥብቅ የደህንነት ክትትል እየተደረገባቸው መሆኑ ተጋለጠ፤**

የወያኔ ቡድን ምዕራባውያንን እና ደጋፊዎቹን ለማታለል ሲል ስልጣኑ ላይ ተረጋግቶ የተቀመጠ ለመምሰል እየጣረ ቢሆንም በውስጥ እና በውጭ በሚገጥመው ከፍተኛ ፈተና ምክንያት ተቸግሮ እንዳለ እና ባለስልጣናቱም በየቀኑ በምስጢራዊ ስብሰባ ተወጥረው እንደሚገኙ ተገለፀ::

የራሴ ናቸው የሚላቸው ከታች እስከ ላይ ድረስ ያሉት ካድሬዎች ከጥቂቶቹ በስተቀር ብዙዎቹ በህዝቡ ላይ በሚደርሰው በደል እና ግፍ እየተበሳጩ በወያኔ ድርጊት ቅሬታ ከማቅረባቸውም በላይ እርስ በርስ እየተነታረኩ እና ስምምነት አጥተው በየቀኑ ግምገማ እያሉ ተወጥረው የሚገኙበት ወቅት መሆኑም ተጠቁሞዋል::

ከወያኔ ቁንጮ ባለስልጣናት ከሆኑት ፖሊት ቢሮ አባሎች ጀምሮ እስከ ወረዳ ካድሬዎች ድረስ በስብሰባና በግምገማ በየቦታው ተወጥረው ያሉበት ወቅት ከመሆኑም በላይ በፍርሀት እና እርስ በርስ በመጠራጠር የሚደረገው ይሄው ግምገማ ከመብዛቱ ና ከመርዘሙ የተነሳ በሳምንት አንድ ቀን እንኩዋን ወደ ቢሮ ገብተው ስራ እንደማይሰሩም ለማወቅ ተችሎዋል::

የወያኔን እድሜ ያራዝማሉ ተብለው ተስፋ ተጥሎባቸው የነበሩት አፍለኛ እና ወጣት ካድሬዎች በአጭር ግዜ የወያኔን መሰሪ ባህሪይ በማወቃቸው የተነሳ እየተበሳጩ በግልፅ በየስብሰባው ላይ ድርጊቱን ከማውገዛቸውም በተጨማሪ ከህዝብ አብራክ ወጥተን በህዝብ ላይ ደባ እና ሸፍጥ አንፈፅምም በማለታቸው በወያኔ ከፍተኛ ባለስልጣናት በኩል ቂም የተቋጠረባቸው መሆኑንም እነዚሁ ወገኖች ተናግረዋል፡፡

ባለፈው ሳምንት እሁድ ዕለት የካቲት 20 ቀን 2003 ዓ.ም በተደረገው የማሙያ ምርጫ ላይ ወጣት ካድሬዎቹ ያልተሳተፉ ሲሆን በምርጫው ላይ እንዲወዳደሩ ተብለው ስማቸው የተመዘገበት ጭምር እንደማያውቁና በተደረገውም እንደማይስማሙ በመግለፃቸው እነ በረከት ክፉኛ እያበዱ መሆኑም ተጋልጦዋል፡፡

ወጣት ካድሬዎቹ የሚያነሱትን ጥያቄ እንዲያዳፍኑ ከመለስ ዜናዊ ተልዕኮ የተሰጣቸው ሬድዋን ሁሴን የተባለው ግለሰብ እና በረከት ስምዖን በቅርብ ሆነው እየተከታተሉ ሲሆን በያዝነው ወር ብቻ እጅግ ቁጥራቸው የበዙትን እንደ አዲስ ለስልጠና በሚል መካኒሳ አካባቢ ወደሚገኘው ደምቦስኮ ካምፕ እያስገቡዋቸውና በግምገማ ሰበብ እያስፈራሩዋቸው እንደሚገኙ ወጣቶቹ ለቤተሰቦቻቸው ሲናገሩ ተደምጦዋል፡፡

የአምስት ዓመቱን የዕድገት እና ትራንስፎርሜሽን እቅድ ተግባራዊ እናደርጋለን እያልን እጃችን እስኪገነጠል ድረስ የመናወዛውዘው በህዝብ ጫንቃ ላይ ልናናጥር ሳይሆን ችግሩን ልንፈታለት ነው ያሉት ወጣት ካድሬዎቹ አሁን እየተደረገና እየተሰራ ያለው ሸፍጥ ግን የትም አያደርሰንም እያሉ በግልፅ ልዩነታቸውን ይፋ ከማድረጋቸውም በተጨማሪ ከቅርብ ግዜ ወዲህ በሰሜን አፍሪካ የህዝብ አመፁ ከተነሳ ወዲህ የልብልብ ተሰምቶዋቸው በድፍረት በየስብሰባው ላይ ቅሬታቸውን እያነሱ መሆኑ ለወያኔ ከፍተኛ ባለስልጣናት ሌላ የራስ ምታት እንደሆነባቸውም ለማወቅ ተችሎዋል፡፡

በተለይ የወያኔ በለስልጣናት ሰሞኑን በተደጋጋሚ ግዜ ከነጋዴው ጋር ውይይት እናድርግ እያሉ ጥሪ ቢያቀርቡም ብዙዎቹ ያልተገኙ ሲሆን በግድ በማስፈራሪያ የተገኙትም ቢሆን ከወያኔ ባለስልጣናት ጋር ውይይት ማድረግ ግዜ ከመፈጀት ያለፈ ቁም ነገር የማይገኝበት እንቶ ፈንቶ ነው ሲሉ ሲያማርሩ ተደምጠዋል፡፡

አንዳንዶቹ ነባር ነጋዴዎች እንደሚሉት ከሆነ ከወያኔ አንዳችም ነገር ስለማናገኝ አንመጣም እያሉ ከመቅረታቸውም በላይ ወያኔ ያወጣውን የዋጋ ተመን አናከብርም በማለት ወያኔን እያስደነገጡት መሆኑም ታውቆዋል፡፡

በዚህም መሰረት ወያኔ የራሱን ሽክም እና ጫና አውርዶ በነጋዴዎቹ ላይ ለመቆለል ከማሰቡም በተጨማሪ ከህዝቡ ጋር ለማጋጨት ሙከራ ቢያደርግም ሳይሳካለት የቀረ መሆኑ የተረጋገጠ ሲሆን ሰሞኑን ደግሞ ነጋዴዎቹ ከውጭ የሚገቡ እቃዎችን ወደ ሀገር ውስጥ አናስገባም በማለት አቁዋም በመያዛቸው ህዝቡ የዕቃ አቅርቦት በማጣቱና ጥያቄ በማቅረቡ የወያኔ ቡድን ከፍተኛ ድንጋጤ ላይ እንደወደቀ ለማወቅ ተችሎዋል፡፡

እስከ ዛሬ ድረስ ነፃ ገበያ በሀገሪቱ እንዲሰፍን የወያኔ ግዙፍ የንግድ ድርጅቶች ለግል ይሸጡ ብለን ብንወተውትም ሰሚ ከማጣታችን ሌላ ይህን ጥያቄ ያነሳ ህገ መንግስቱን ለመናድ ሙከራ ያደረገ ነው እየተባልን ለእስር ስንዳረግና ስንቀጣ ነበርን ያሉት ነጋዴዎቹ ይህ ባልሆነበት እና የነፃ ገበያ ውድድር ባልሰፈነበት ብሎም ይፋ አድልኦ በተንሰራፋበት በዚህ ግዜ ገበያ ለማረጋጋት ውይይት እናድርግ ብሎ ስብሰባ መጥራት ከቀልድ አያልፍም ሲሉ ነጋዴዎቹ በምሬት ሲገልፁ ተደምጠዋል።

የወያኔ ግዙፍ የንግድ ድርጅቶች እንደማንኛውም የንግድ ተቁዋም ተወዳድረው መስራት ሲገባቸው ከዚህ ቀደም ከሚፈፅሙት ምዝበራና ወንጀል በተጨማሪ ያለ ቀረጥ እና ግብር እቃ እያስገቡ ሲቸበችቡ እኛ ቀረጥና ግብር እየከፈለን በመሸጥ ስንታገል ብንቆይም በተጨባጭ እየታየ ያለው ሁኔታ ግን ጨርሶ የማያሰራ በመሆኑ በፍፁም ከውጭ እቃ አናስመጣም ስራም እናቆማለን በማለት ነጋዴዎቹ አቁዋም በመያዛቸው ወያኔ በፍርሀት እየራደ መሆኑ ተጠቁሞዋል።

ጉዳዩ ያስደነገጠው የወያኔ ቡድን ከመሪው መለስ ዜናዊ ጀምሮ እስከ ክልል ብሎም ክፍለ ከተማ አመራሮች ድረስ በተከታታይ ቀናት ነጋዴዎቹን ሰብስበው ውይይት ቢያደርጉም አንድም የረባ ስምምነት ላይ ሳይደርሱ ከመቅረታቸውም በላይ ነጋዴዎቹ ከቅርብ ግዜ ወዲህ ጠንከራ አቁዋም እየያዙ በመምጣታቸው የወያኔ ባለስልጣናት ምን ማድረግ እንደሚገባቸው እና መወሰን እንዳለባቸው ተቸግረው እንደሚገኙም ተነግሮዋል።

ከውጭ የሚመጡ ዘይት እና ሌሎች ቁሳቁሶችን የግል ኩባንያዎች የሚያስመጡ የነበረ ቢሆንም ወያኔ ከግምት ውስጥ ሳያስገባ ባወጣው የዋጋ ተመን እጅግ ከፍተኛ ኪሳራ ያደረሰብን ከመሆኑም በተጨማሪ ለደረሰብን ኪሳራ አንዳችም ድጎማ ያላደረገልን ከመሆኑም በላይ እሱ ያጠፋውን ጥፋት በእኛ ላይ ለጥፎ የፍየል ወጠጤን ሊዘፍንብን ይፈልጋል እያሉ በብስጭት እየተናገሩ ያሉት ነጋዴዎቹ የወያኔ ግዙፍ የንግድ ኩባንያዎች ነጋዴውን አላሰራ ብለው ባሉበት በዚህ ወቅት እንደገና ከገዛነው በታች እንድንሸጥ ሆን ብለው የዋጋ ተመን ማውጣታቸው እንድንከስር እና በዶ እጃችንን እንድንቀር ብሎም ስንዴና ዘይት እርዳታ ጠያቂ ሆነን እንድንቀር ታስቦ የሚሰራ ተንኮል ነው ሲሉ በምሬት ሲገልፁ ተደምጠዋል።

በተለይ በ1997 ዓ.ም በተደረገው የሀገር አቀፍ ምርጫ ወቅት ለተቃዋሚዎች ከፍተኛ ገንዘብ ድጋፍ ሲያደርጉ የነበሩት ነጋዴዎች ናቸው በሚል በጥላቻ አይን እያየን በመሆኑ አሁንም ያንን ቂም በመያዝ ወደ ድህነት አረንቋዋ ሊከተን እያሰበ መሆኑን ህዝብ ሊያወቅልን እና ሊገነዘብልን ይገባል ሲሉም ጨምረው ገልፀዋል።

በቅርቡ ህዝቡ ከኑሮ ወድነት ሸክሙ እንዲቃለልለት በሚል የዋጋ ተመን ወጥቶ ሁሉም ነጋዴ በኪሳራም ቢሆን እንድንሸጥ ተስማምተን የተወሰነ ግዜ ብንጀምርም በተጉዋዳኝ ግን የወያኔ የንግድ ኩባንያዎች በጎን በኩል ከገበያ ያለቁና የጠፉ እቃዎችን አስመጥተው ከተመን ዋጋ ውጭ እየቸበቸቡ መሆኑን በውይይቱ ላይ ለመለስ ዜናዊ ብንነግረውም ከአፍ ያልዘለለ የይምሰል ምላሽ ሰጠን እንጂ አንዳችም የተወሰደ እርምጃ የለም ያሉት ነጋዴዎቹ አሁን ግን ትግላችን የሞት ሽረት በመሆኑ በራሳችን መንገድ ከህዝቡ ጋር በመሆን በወያኔ ላይ እንዘምታለን ሲሉም ተናግረዋል።

አንድ ለግዜው ስማቸው እንዲገለፅ ያልፈለጉ አንጋፋ ነጋዴ እንዳሉት ከሆነ ዛሬ በተለይ በመርካቶ ውስጥ የሚሰራ ነጋዴ በወያኔ ላይ እምነት ስለሌለው ገንዘቡን ሁሉ አውጥቶ በውጭ ሀገር እያስቀመጠ ሲሆን ለይምሰል ብቻ ጥቂት መንቀሳቀሻ ብቻ ይዞ እየተወዛወዘ እንደሚገኝ ገልፀዋል።ይሄንኑ ሀሳብ ሲያጠናክሩም ችግሩ የመጣው ከራሱ ከወያኔ በኩል ነው ያሉት እኚሁ ነጋዴ ባለስልጣናቱ ከህዝብ እና ከሀገር የዘረፉትን ገንዘብ ወደ ውጭ እየላኩት መልሰው በእኛው እና በህዝቡ ገንዘብ ከጥቂት ሰላይ ነጋዴዎች ጋር በመመሳጠር እየሰሩበት ሲሆን እንደዜጋ በነፃነት ያፈራነውን ሀብት እዚሁ ብንሰራበት ብንችል በጣም ጥሩ ነበር ነገር ግን ወደፊት የህዝብ ገንዘብ ዘርፋችሁ ነው ያጠራቀማችሁት ብሎ ሊነጥቀን የማይችልበት አንዳችም ምክንያት የለም ሲሉም በወያኔ ላይ እምነት እንደሌላቸው አፅንኦት ሰጥተው ገልፀዋል።

ዛሬ ኑሮ ውድነቱ በከፍተኛ ሁኔታ በህዝቡ ውስጥ ተንሰራፍቶ ባለበት ወቅትና በቂ የእቃ አቅርቦት ሳይኖር የወያኔ ቡድን በግዴታ ነጋዴውን እንዲሸጥ ማስገደዱ ሆን ብሎ ነጋዴውን ከህዝቡ ለማጋጨት እና ለማበጣበጥ እያደረገ ያለው ሴራ መሆኑን የጠቆሙት እኚሁ ነባር የመርካቶ ነጋዴ ሰሞኑን የአንድ ኪሎ ቡና ዋጋ መቶ ብር እና ከዛ በላይ እንዲሆን ያደረገው እራሱ ወያኔ ሆኖ ሳለ በኛ ላይ ጣቱን ሊቀስር መሮጡ የሚያሳዝን እና የሚያሳፍር ነው ብለዋል።

የንግድ ገበያ በሚል እራሱ ባቋዋቋዋመው የገንዘብ መሰብሰቢያ ድርጅት ነጋዴው በራሱ ግዜ እንደቀድሞው ከገበሬው ገዝቶ እንዳይሸጥ ማዕቀብ ጥሎ ከየሀገሩ እያግበሰበሰ ወደ ውጭ እየላከ በቀን በሚሊዮን የሚቆጠር ዶላር እያፈሰ ዛሬ የቡና አቅርቦት ከሀገር ውስጥ እንዲጠፋ አድርጎ በ30 ብር ሲሸጥ የነበረውን የአንድ ከሎ ቡና ዋጋ ከአንድ መቶ ብር በላይ እንዲያሻቅብ አድርጎ መልሶ በነጋዴው ላይ ሊያፈጥ መነሳቱ የሚያሳዝን ድርጊት ነው ሲሉም በምሬት ሲናገሩ ተደምጠዋል።

ሰሞኑን ነጋዴዎቹ እቃዎችን ወደ ሀገር ውስጥ አናስገባም የሚል አቋም በመያዛቸው ምክንያት ብዙዎቹ እቃዎች ከገበያ ከመጥፋታቸውም በተጨማሪ ዋጋቸው እየተቆለለ ወያኔ ያወጣውን የዋጋ ተመን ተግባራዊ ያላደረገ የግብይይት ስርዓት ሲካሄድ የሰነበተ ሲሆን አንድ ኪሎ ስኩዋር ወያኔ 14 ብር ሽጡ ያላቸውን እነሱ 15 ብር እየሸጡ ሲሆን.....ዘይት 420 ብር ሽጡ ያላቸውን 500 ብር እየሸጡ እንደነበርና ይሄንንም ከተከለከልን ስራ እናቆማለን እያሉ እንደሚገኙ ታውቆዋል።

ወያኔ በበኩሉ የህወሀት ንብረት በሆኑት የንግድ ድርጅቶች አማካኝነት ወደ ሀገር ውስጥ የሚገቡትን እቃዎች ሙሉ ለሙሉ በእነሱ ሊያስገባና ነጋዴዎችን ከጨዋታ ውጭ ሊያደርጋቸው እየተዘጋጀ ከመሆኑም በላይ ነጋዴዎቹን አድማ አድርጋችሁዋል በሚል ወደ እስር ቤት ሊወረውራቸው በምስጢር እየሰራ መሆኑ ተጋልጦዋል።

የህዝቡን ጥያቄ ወደ ጎን ትተው ለራሳቸው ዝና እና ለቤተሰቦቻቸው ክብር ብቻ ሲጨነቁና ሲንደላቀቁ ብሎም ሲንፈላሰሱ የኖሩት የዐረብ ሀገራት መሪዎች በተለይ የሊቢያው መሪን ጨምሮ ሌሎቹም ህዝብ ኑሮው ከአቅሙ በላይ ሲሆን በወሰደው ቆራጥ እርምጃ ነፃነቱን እንደተቀዳጀ ሁሉ የወያኔም ባለስልጣናት በሀገር እና በህዝብ ላይ ሲቀልዱና ሲያሾፉ አንዳልነበር ህዝብ ቆርጦ የተነሳ ግዜ ማጣፊያው እንደሚያጥራቸው ጥርጥር የለንም ሲሉም ነጋዴዎቹ በምሬት እየተናገሩ ይገኛሉ።

በሌላ ዜና የወያኔው ዋና አቀንቃኝ የነበረውና ከስልጣኑ የተባረረው ኮማንደር ደምሳሽ ኃይሉ የተባለው የፌዴራል ፖሊስ የህዝብ ግንኙነት ኃላፊ የነበረው ግለሰብ ድንገት ከሀገር ወጥቶ መኮብለሉ ታወቀ።

ከወያኔ ከፍተኛ ባለስልጣናት ጋር እጅግ ቀረቤታ የነበረውና በ1997 ዓ.ም ምርጫ ወቅት በንፁሀን ዜጎች ላይ ዘረኛውና ጨፍጫፊው የፌዴራል ፖሊስ ዘግናኝ እርምጃ ሲወስድ በነበረበት ወቅት ሰፊ ሽፋን ሲሰጥ የነበረውና በወያኔዎች ሲወደስ እና ሲሞካሽ የነበረው ኮማንደር(ኮሎኔል) ደመሳሽ ከጊዜ ወደ ግዜ ከአለቆቹ ከእነ ወርቅነህ ገበየሁ እና ከነሐሰን ሽፋ ጋር በፈጠረው አለመግባባት የተነሳ ከስልጣኑ እንዲወርድ ተደርጎ ለቀናት በማዕከላዊ እስር ቤት ታስሮ እንደነበር ይታወቃል።

ከማዕከላዊ እስር ቤት ከተፈታ በሁዋላም በደህንነት ከፍተኛ ክትትልና ቁጥጥር ሲደረገበት የነበረው ይሄው ግለሰብ በሙስና ክስ ተከስሶ የነበረና በሌላም ክስ በጠቅላይ ፍርድ ቤት ሲፈለግ የነበረው ደመሳሽ ድንገት ባልታወቀ መንገድ ከሀገር ጠፍቶ ወደ ውጭ ሀገር ከመኮብለሉም በተጨማሪ ጥገኝነት መጠየቁ ለቤተሰቦቹ ቅርበት ካላቸው ወገኖች ጥቆማ ለማወቅ ተችሎዋል።

በስልጣን ላይ በነበረበት ግዜ ከከፍተኛ የወያኔ ባለስልጣናት ጋር ቀረቤታ የነበረው ይሄው ግለሰብ ብዙ እና የተደበቁ ምስጢሮችን የሚያውቅ በመሆኑ አሁን ከሀገር ከወጣ በሁዋላ ሊያጋልጠንና ምስጢሮችን ሊያዝረከርክ ይችላል በሚል ስጋት የወያኔ ባለስልጣናት እየታመሱ መሆኑም ታውቆዋል።

በ1997 ዓ.ም ህዝባዊ ምርጫ ተደርጎ የወያኔ በድን መሉ ለሙሉ ተሸነፎ በተባረረበት ወቅት........ ህዝብ ድመጼ ይከበር ብሎ ሰላማዊ ጥያቄ በማቅረብ ባለበት ግዜ....... የፌዴራል ፖሊስ እና ቀይ ቆብ ያጠለቁ ሰው በላ አረመኔ የወያኔ ቅጥረኛ ወታደሮች በጋራ በመሆን ዘግናኝ ጭፍጨፋ ሲያደርጉ ሲከታተል እንደነበርና ይሄንን እና ሌሎች የተደበቁ ምስጢሮችን ሊያጋልጥ ይችላል በሚል ፍርሀት ሰሞኑን የወያኔ ከፍተኛ በለስልጣናት እየታመሱ ሲሆን ከቦሌ አውሮፕላን የደህንነት ሰራተኞች መሀከልም ግንኙነት ነበራችሁ የተባሉ በጥርጣሬ እየተያዙ ለጥያቄ እየቀረቡ መሆኑ ታውቆዋል።

ይሄው ግለሰብ የፌዴራል ፖሊስ የህዝብ ግንኙነት ኃላፊ ሆኖ በሚሰራበት ወቅት በአዲስ አበባና በሌሎች ከተሞች በፌዴራል ፖሊስ እና በወታደሮች ጥምረት የተወሰደውን ግድያና በምስጢር ስለተደረጉት የአስከሬን ቀበራ ምስጢር የሚያውቅ በመሆኑ ይህንኑ አጋልጦ ገመናችንን ያዝረከርከዋል በሚል ድንጋጤ ባለስልጣናቱ እርስ በርስ እየተወነጃጀሉ እንደሚገኙም ታውቆዋል።

አዲስ አበባን ጨምሮ በተለያዩ ከተሞች ውስጥ የተፈጸሙ ምስጢራዊ ግድያዎችን እና እስከ አሁን ድረስ ብዙ ዜጎች የደረሱበት ያልታወቁ መሆኑን እንደሚያውቅ ያጋለጡት ለቤተሰቦቹ ቅርበት ያላቸው ወገኖች የሚያውቀውን ምስጢር ጥገኝነት በጠቀየቀበት እንግሊዝ ሀገር ሊያጋልጥ ይችላል በሚል ፍርሀት በተለይ በደህንነት ባለስልጣናት መሀከል ንትርክ መጀመሩን አጋልጠዋል።

ከስልጣኑ እንደተባረረ በከፍተኛ ፍርድ ቤት የሙስና ክስ ቀርቦበት በነፃ የተሰናበተ ሲሆን በነፃ ያሰናበተው ዳኛም ለግዜው ከቦታ ወደ ቦታ እንዲዘዋወር እየተደረገ ከመሆኑም በላይ አሁን ድረስ ቋሚ ችሎት ያልተሰጠው መሆኑንም ከውስጥ አዋቂ ምንጮች የደረሰን ጥቆማ አጋልጦዋል።

በተለይ ከየቤታቸው እየተለቀሙ እየተወሰዱ ባልታወቀ ቦታ እየተገደሉ የሚጣሉትን ዜጎች ማን እንደገደላቸው እና የት ቦታ እንደተገደሉ በግልጽ እንደሚያውቅ ያጋለጡት እነዚሁ ወገኖች እስከ ዛሬ በውድም ሆነ በግዴታ የሰራቸውንና የሚያውቃቸውን ብዙ ምስጢሮችን ማጋለጥ ግድ ይለዋል ሲሉም ምክር አዘል ሀሳብ ሰንዝረዋል፡፡

በቅርቡ በጠቅላይ ፍርድ ቤት አዲስ ክስ ተመስርቶበት የመያዣ ትዕዛዝ ተቆርጦበት ሲፈለግ የነበረው ደምሳሽ አስቀድሞ በደረሰው መረጃ መሰረት ድንገት ከሀገር በመውጣቱ የተበሳጩት የደህንነት ባለስልጣኑ ጌታቸው አሰፋ እና ሌሎች ከፍተኛ የደህንነት ሹሞች በመስሪያ ቤቱ መምሪያ ኃላፊዎች ላይ ከፍተኛ ግምገማ ያደረጉባቸው ከመሆኑም በላይ በቦሌ አውሮፕላን ማረፊያ ሲሰሩ የነበሩትን የደህንነት አባሎች ሲወጣ ለምን ዝም አላችሁ በሚል ቃላቸውን እንዲሰጡ ተደርገው እያስፈራሩዋቸው መሆኑ ታውቆዋል፡፡

ከዚህም በተጨማሪ በስራ ላይ በነበረበት ወቅት አብዛኛዎቹ ጉዋደኞቹ የፖሊስ ኮሌጅ ምሩቃን የነበሩ ከመሆኑም በተጨማሪ ለቀድሞ መንግስት ያገለገሉ በአሁኑ ግዜም እየሰሩ የሚገኙ ቢሆኑም ከደምሳሽ ጋር እጅግ የቀረበ ግንኙነት አላቸው በተባሉት መኮንኖች ላይ የደህንነት ሰዎች ከሚሰሩበት እስከ መኖሪያ ቤታቸው ድረስ በየቀኑ ክትትል እየተደረገባቸው እንደሚገኙ እነዚሁ ቅርበት ያላቸው ወገኖች ገልፀዋል፡፡

ባለፈው ሳምንት በወያኔ ውስጥ ያለውን ውጥረት ለማስተንፈስ ሲባል የከፍተኛ መኮንኖች የማዕረግ እድገት በተሰጠበት ወቅት ከ80 በመቶ በላይ ከበረሀ ለመጡት የወያኔ አባሎች ሲሆን እስከ ዛሬ በሀገሪቱ ታሪክ ታይቶና ተሰምቶ ባልታወቀ ሁኔታ ለአንዲት በረሀ አመጣሽ ታጋይ የጄኔራልነት ማዕረግ እንደተሰጣትና ህዝቡን እንዳስገረመ አይዘነጋም፡፡